# ማተብህን በጥሰህ

ከአሊ ሁሴን

በውድቅት ሌሊት በዛ ጠፍ ጨረቃ
ዶሮ ሶስቴ ሳይጮህ ታዳሚው ሳይነቃ
እንደነ ጲላጦስ ፣ እንደነ ይሁዳ
እየሱስን ክደው
አሳልፈው ሰጥተው
እንዳስፈረዱበት ውግረትና ስቅለት፣

አንተም

ማተብህን በጥሰህ
እምነትህን አውልቀህ
ክህደትን ተላብሰህ
ቅራቅንቦችህን ሰብስበህ ቀርቅበህ
ካደርክበት እልፍኝ ከዚያ ከትግል ቦታ
የነተስፋዬን ቤት የነአበራሽ በርታ
የፀጋዬን  ቤት የጋይም የዳፍላን
የነይሰሃቅን ቤት የነ ውብሸት ረታን
የነማርቆስን ቤት የኢብራሂም ሚፍታን
ፅናት እምነት እርቆህ አፍርሰህ ማሃላ
ለነጭ ለጥቁር ጅብ ለምድረ ተኩላ
መሰረት አናግተህ
መዝጊያውን ነቃቅለህ
ከፍተህ ልታስበላን
ወድህ ወዲያ ስትል
ቢሰማ ሹክሹክታ
ከከህደት   ኃላ የትሳኤው ለታ
የነቃ የበሰለው ያ ሁሉ እድምተኛ
አይቶህ እንዳላየ መስሎህ እንደተኛ
እምነቱን ሳይነካ
ክብረቱን ሳይነጥቅህ
መወቀስን ጠልተህ
ምላሹን ሳይሰጥህ
ልክ እንደዳቢሎስ
ስልብ በማለትህ
እድምተኛው ሁላ

ብሎ ዘፈነብህ፣

ሃሙስ ፈረደና
አርብ ቀን ሰቀለ
ቅዳሜ አድብቶ
እሁድ ኮበለለ

ሂደ አሉ ሳይነጋ
ሂደ አሉ ሳይነጋ
ሂደ አሉ ሳይነጋ

ወንበሩን ፍለጋ።

ሂደ አሉ ለባብሶ
ሂደ አሉ ለባብሶ
ሂደ አሉ ለባብሶ

የአንጃ ቤት ቀልሶ።

ሂደ ተቀብቶ
ሂደ ተቀብቶ
ሂደ ተቀብቶ

የአንጃ ዙፋን ሰርቶ።

አነሰ እንደ ጳጉሜ
አነሰ እንደ ጳጉሜ
አነሰ እንደ ጳጉሜ

በአለቀለት እድሜ
ሳይገባ ሱባዔ
ከድምተኛው አፍሮ ሸሸ ከጉባዔ።

ባለቀልህ እድሜ
በመሂጃህ ጨርቆስ
ክህደት ካሸነፈህ
በል እንግዲህ አዲዮስ!!!!!